EDITION 2026

# የ2026 የScholarship መመሪያ

ህልምህ ከወሰን እንዲያልፍ...
ዓለም አቀፍ ዕድሎችን በነፃ የማግኛ ሚስጥራዊ ቁልፍ።



**አዘጋጅ: ScholarshipHub.website**

# የቅጂ መብት © 2026 ScholarshipHub

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በነፃ እንዲሰራጭ ነው። እውቀት ሲካፈል ይበዛል! ለጓደኛዎ፣ ለቤተሰብዎ ወይም ለሚወዱት ሰው በነፃ ያካፍሉ።


***"ይህ መጽሐፍ፣ ያሉበት ሁኔታ ሳይገድባቸው***
***የራሳቸውን የህይወት ታሪክ በአዲስ መልክ ለመጻፍ ለሚፈልጉ***
***ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተማሪ የተበረከተ ነው።"***


ለበለጠ መረጃ፡ t.me/scholarshiphubwebsite

scholarshiphub.website

# የይዘት ማውጫ


1. መግቢያ: የዕድሎች ዓለም 04

2. የአስተሳሰብ ለውጥ (Mindset) 05

3. ወሳኝ ሰነዶች (Checklist) 06

4. ፓስፖርት እና ትራንስክሪፕት 07

5. CV እና Resume (Europass) 09

6. አሸናፊ Motivation Letter 12

7. የ Recommendation ሚስጥሮች 16

8. ያለ IELTS የሚሰጡ ሀገራት 20

9. ነፃ ዩኒቨርሲቲዎች (No Fee) 30

10. የ ፕሮፌሰሮች ኢሜይል 35



**አዳዲስ ስኮላርሺፖች ሲወጡ ማወቅ ይፈልጋሉ?**

የቴሌግራም ቻናላችንን ይቀላቀሉ:
**t.me/scholarshiphubwebsite**


scholarship.website

# 1. ሰላም ወዳጄ! (መግቢያ)



ይህንን መጽሐፍ ስትከፍት በውስጥህ ትንሽ ፍርሃት ወይም ጥርጣሬ ሊኖር ይችላል። **"እውነት ይሳካልኝ ይሆን?"**፣ **"ውድድር አይበዛም?"** ብለህ አስበህ ይሆናል። ግን አንድ ነገር ልንገርህ... አሁን ይህንን እያነበብክ ነው ማለት፣ ህይወትህን ለመቀየር የመጀመሪያውን እና ወሳኙን እርምጃ ወስደሃል ማለት ነው።

ብዙዎቻችን ያደግነው "ውጪ ሀገር መማር የሀብታም ልጆች ወይም የጂኒየሶች እድል ነው" ተብለን ነው። ይህ ትልቅ ውሸት ነው። እውነታው ግን፣ በየዓመቱ በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር በጀት ተማሪዎችን እየፈለገ ባክኖ ይቀራል። ችግሩ የገንዘብ እጥረት ሳይሆን፣ **የመረጃ እጥረት** ነው።

> *"ዕድል (Luck) ማለት ዝግጅት እና አጋጣሚ ሲገናኙ የሚፈጠር ነገር ነው። ዝግጅት ከሌለህ፣ አጋጣሚው ቢመጣም አታየውም።"*

ይህ መጽሐፍ ዝም ብሎ የመረጃ ክምር አይደለም። ይህ መጽሐፍ ያንተ **"የስኬት ካርታ"** ነው። በጨለማ ውስጥ እንዳትዳክር፣ ትክክለኛውን ዩኒቨርሲቲ ከመምረጥ ጀምሮ፣ እራስህን በወረቀት ላይ እንዴት እንደምትገልፅ እና ያለምንም ወጪ እንዴት ማመልከት እንደምትችል እጅህን ይዤ አሳይሃለሁ።

**ጉዞውን ለመጀመር ዝግጁ ነህ? እንቀጥል...**

# 2. አስተሳሰብህን አስተካክል (Mindset)

ማመልከቻ (Application) ከመሙላትህ በፊት፣ አእምሮህን ማዘጋጀት አለብህ። ብዙ ጎበዝ ተማሪዎች የሚወድቁት በውጤት ማነስ ሳይሆን፣ **በአስተሳሰብ ስህተት** ነው። እባክህ እነዚህን ሁለት እንቅፋቶች ከአእምሮህ አውጣ፡

### የተሳሳተ እምነት 1: "GPA (ውጤት) ብቻ ነው የሚወስነው"

እርግጥ ነው፣ ጥሩ ውጤት መያዝ ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ብቸኛው መመዘኛ አይደለም። በ **2.8 እና 3.0 GPA** ሙሉ ስኮላርሺፕ ያገኙ ተማሪዎች እንዳሉ ታውቃለህ? ዩኒቨርሲቲዎች የሚፈልጉት "ሮቦት" ሳይሆን "ሰው" ነው። ከትምህርት ውጪ ምን ሰርተሃል? ያንተ ታሪክ (Story) ከውጤትህ የበለጠ ዋጋ አለው።

### የተሳሳተ እምነት 2: "እኔ እንግሊዝኛ አልችልም"

ቋንቋ መግባቢያ መሳሪያ እንጂ የብልህነት መለኪያ አይደለም። ስኮላርሺፕ ለማግኘት እንደ አሜሪካዊ ማውራት አይጠበቅብህም። ሀሳብህን በግልጽ በወረቀት ላይ ማስፈር ከቻልክ በቂ ነው።

**እራስህን ጠይቅ: "ለምን መማር ፈለግኩ?"**

መልስህ "ሀገር ጥሎ ለመጥፋት" ከሆነ ስኮላርሺፕ ማግኘት ይከብድሃል።
መልስህ **"ችግር ፈቺ ለመሆን እና ተጽዕኖ ለመፍጠር"** ከሆነ፣ መንገዱ ክፍት ይሆንልሃል።

# 3. መሳሪያህን አዘጋጅ (Document Checklist)



ወደ ጦርነት የሚሄድ ወታደር መሳሪያውን እንደሚፈትሽ ሁሉ፣ ወደ ስኮላርሺፕ ዓለም የሚገባ ተማሪም ሰነዶቹን መፈተሽ አለበት። ማመልከቻ ከመጀመርህ በፊት እነዚህ **5 ወሳኝ መሳሪያዎች** በእጅህ ሊኖሩ ይገባል።

### 1. ፓስፖርት (Passport)

ጊዜው ያላለፈበት እና ቢያንስ ለቀጣይ 1 አመት የሚያገለግል።

### 2. የትምህርት ማስረጃ (Transcripts)

ኦፊሴላዊ (Official) ትራንስክሪፕት እና የዲግሪ ሰርተፍኬት።

### 3. CV / Resume (Europass)

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የሥራ ታሪክ መግለጫ።

### 4. Motivation Letter (SOP)

ማንነትህን እና ራዕይህን ለኮሚቴው የምትሸጥበት ድርሰት።

### 5. Recommendation Letters

ከሁለት መምህራን የተጻፈ ጠንካራ የድጋፍ ደብዳቤ።

***ማሳሰቢያ:*** *እነዚህ ሰነዶች ሳይሟሉ ማመልከቻ መጀመር ማለት ጊዜን ማባከን ነው። ዛሬውኑ ማሟላት ጀምር!*

scholarship.website

# 4. ፓስፖርት እና ትራንስክሪፕት

## ሀ. ፓስፖርት (Passport)

ብዙ ተማሪዎች "ስኮላርሺፑን ካገኘሁ በኋላ ፓስፖርት አወጣለሁ" ይላሉ። ይህ **ትልቅ ስህተት** ነው።

✓ አብዛኛዎቹ የኦንላይን አፕሊኬሽኖች አካውንት ለመክፈት የፓስፖርት ቁጥር ይጠይቃሉ።

✓ ፓስፖርት ለማውጣት የሚፈጀውን ጊዜ ታውቃለህ፤ እድሉ ከመጣ በኋላ መሯሯጥ ውድቀት ነው።

> **⚠ ማስጠንቀቂያ:**
>
> ፓስፖርትህ አገልግሎቱ ሊያበቃ (Expire ሊያደርግ) ከ6 ወር በታች ከቀረው፣ በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት ለጉዞ አይሆንም። አሁኑኑ ያድሱ።

---

## ለ. ትራንስክሪፕት (Transcripts)

ሁለት አይነት ትራንስክሪፕት አለ፡ "Student Copy" እና "Official Transcript"። ለስኮላርሺፕ የሚያስፈልገው **Official Transcript** ነው። ይህንን ከሬጅስትራር፣ ማህተም ተደርጎበት ማግኘት አለብህ።

> 💡 **የቃኝ (Scanning) ጥበብ:**
>
> ዶክመንቶችህን ስካን ስታደርጉ በስልክ ካሜራ ("CamScanner") ከመጠቀም ይልቅ በስካነር ማሽን (Printer Scanner) ተጠቀም።
>
> - **ፎርማት:** ሁልጊዜ PDF ተጠቀም (Image/JPG እንዳትጠቀም)።
> - **ጥራት:** ፋይሉ ንፁህና የሚነበብ መሆን አለበት።
> - **ስም:** ፋይሉን ስትሰይም ግልጽ ይሁን።
>   *(ለምሳሌ: Abebe_Kebede_Transcript.pdf)*

ship.website

# 5. ዓለም አቀፍ CV (Europass)




ጓደኛዬ፣ የኢትዮጵያ ስታንዳርድ CV ለውጪ ሀገር አይሰራም። ለምሳሌ በኢትዮጵያ CV ላይ ስለ ሃይማኖት፣ ጾታ፣ እና እድሜ መጻፍ የተለመደ ነው። በአውሮፓ እና በአሜሪካ ግን ይህ እንደ **አድሎ (Discrimination)** ስለሚቆጠር አያስፈልግም።

## Europass CV ምንድን ነው?

**Europass** የአውሮፓ ህብረት ያዘጋጀው ወጥ የሆነ የ CV ፎርማት ነው። አብዛኛዎቹ የአውሮፓ ስኮላርሺፖች (እንደ Erasmus Mundus, DAAD, Chevening) የሚፈልጉት ይህንን ፎርማት ነው። ነፃ ነው፣ ንፁህ ነው፣ እና ተቀባይነት አለው።

**Europass CV ለመስራት እዚህ ይጫኑ**

## የ CV ህጎች (Do's and Don'ts)

### አድርግ (Do's)

- **GPA ጥቀስ:** ውጤትህ ጥሩ ከሆነ (ከ3.0 በላይ) በግልጽ አስቀምጠው።
- **ተግባር ተኮር ቃላት:** "Managed", "Created", "Led" የሚሉ ቃላትን ተጠቀም።
- **PDF ብቻ:** በ Word (Docx) አትላክ፣ ፎርማቱ ሊዛባ ይችላል።

### አታድርግ (Don'ts)

- **ፎቶግራፍ:** አሜሪካ እና ካናዳ ስታመለክት ፎቶ አታድርግ (አውሮፓ ይቻላል)።
- **የግል መረጃ:** ስለ ትዳር ሁኔታ፣ ሃይማኖት አትጻፍ።
- **ከ2 ገፅ መብለጥ:** ለ Master's አመልካች ከ2 ገፅ በላይ CV አያስፈልግም።

# 5. ለ. የ CV ናሙና (Sample)

ጥሩ CV ምን ይመስላል? በቃላት ከመግለጽ በተግባር ማየት ይሻላል። ከዚህ በታች ያለው ናሙና በአውሮፓ ስታንዳርድ (Europass) መሰረት የተዘጋጀ **"አሸናፊ CV"** ነው።

## ABEBE KEBEDE

Addis Ababa, Ethiopia | +251 911 234 567 | abebe.kebede@gmail.com

LinkedIn: linkedin.com/in/abebe-kebede

---

**EDUCATION**

**B.Sc. in Civil Engineering** | Addis Ababa University

*Sep 2019 - Jul 2024*

- Cumulative GPA: **3.85 / 4.00** (Graduated with Distinction)
- Thesis: "Sustainable Low-Cost Housing Materials for Urban Ethiopia"

**WORK EXPERIENCE**

**Junior Site Engineer** | Rama Construction PLC

*Aug 2024 - Present*

- Supervised a team of 20 workers on a G+10 building project.
- Reduced material wastage by 15% through strict monitoring using Excel.

**SKILLS**

- **Languages:** Amharic (Native), English (C1 - Advanced)
- **Software:** AutoCAD, ETABS, MS Project

💡 **ማስታወሻ:** ይህ አጭር ናሙና ነው። የራስዎን CV ለመስራት ወደ **ScholarshipHub.website** ይሂዱና ሙሉውን ቴምፕሌት ያውርዱ።

# 6. አሸናፊ Motivation Letter (SOP)



ይህ የስኮላርሺፕ አፕሊኬሽን **"ልብ" (Heart)** ነው። ኮሚቴው እናንተን በአካል አያያችሁም። ውጤታችሁ ወረቀት ላይ ያለ ቁጥር ብቻ ነው። እናንተን "ሰው" የሚያደርጋችሁ እና ከሌሎች በሺዎች ከሚቆጠሩ ተማሪዎች የሚለያችሁ ይህ ደብዳቤ ነው።

## Motivation Letter ምንድን ነው?

በቀላል አማርኛ፣ ለሚከተሉት 3 ወሳኝ ጥያቄዎች መልስ የምትሰጡበት ድርሰት ነው፡

**Why You?**
ለምን አንተን እንምረጥ?

**Why Us?**
ለምን እኛን መረጥክ?

**Future Plan?**
ለሀገርህ ምን ትሰራለህ?

scholarship.we

# 6. ሀ. አጀማመር (The Hook)

የመጀመሪያው ፓራግራፍ (Introduction) አንባቢውን ካልማረከው፣ ቀጣዩን ላያነብ ይችላል። ስለዚህ እንደ "ፊልም" ጀምሩት። **ችግርን (Problem)** በማውራት ጀምሩ።

**የተለመደ ስህተት (Boring):**

"My name is Abebe. I was born in 1999 in Addis Ababa. I am applying for the Master's in Public Health because I want to help my country. I have a degree from Jimma University with a good GPA."

**(ይህ በጣም አሰልቺ ነው። ኮሚቴው ስምህን ከ CV ላይ ማንበብ ይችላል።)**

**የሚማርክ አጀማመር (Storytelling):**

"Growing up in rural Ethiopia, I witnessed my aunt suffer from a treatable disease simply because the nearest clinic was 50km away. That day, standing by her bedside, I realized that the problem wasn't a lack of medicine, but a lack of healthcare policy. This is why I want to study Public Health."

**(ይህ ስሜት ይነካል። ኮሚቴው "Wow, this student has a purpose" ብሎ ያስባል።)**

scholar

# 6. ለ. የ SOP ናሙና (Template)

አንዴ ከተዋወቃችሁ በኋላ፣ ብቃታችሁን ማሳየት አለባችሁ። ዝም ብላችሁ "ጎበዝ ነኝ" አትበሉ። በማስረጃ አስደግፉ። ከዚህ በታች ያለው ወርቃማ ናሙና ነው።

**TO: The Selection Committee**
**RE: Statement of Purpose for M.Sc. in [Your Field]**

[The Hook - ችግሩን ማውራት]
Three years ago, while working as a junior engineer in Addis Ababa, I noticed a critical failure in our drainage systems during the rainy season. Seeing the city flood made me realize that Ethiopia needs sustainable infrastructure solutions. This experience is the driving force behind my decision to pursue a Master's in Civil Engineering.

[Academic Background - ብቃትህን ማሳየት]
During my undergraduate studies at [University Name], I focused on structural integrity. My thesis, titled "[Thesis Title]," analyzed local building materials. I graduated in the top 5% of my class, which demonstrates my academic dedication.

[Why This University? - ስለ እነሱ ማውራት]
I have chosen [University Name] because of your advanced curriculum in Urban Planning. I have read the works of Dr. [Professor Name] regarding sustainable cities, and I am eager to learn from his expertise.

[Future Plan - ትርፉ ምንድን ነው?]
Upon returning to Ethiopia, my goal is to work with the City Administration to design flood-resistant infrastructure. This scholarship will give me the technical skills to make this vision a reality.

Sincerely,
[Your Name]

⚠ **ማስጠንቀቂያ:** ይህንን ናሙና እንደ መነሻ (Reference) ተጠቀሙበት እንጂ በቀጥታ ኮፒ አታድርጉት። **Plagiarism (ኮፒ)** ከተገኘባችሁ እድሉ ይሰረዛል።

# ይህ ናሙና (Preview) ብቻ ነው!

ውድ ተማሪ፣ እስካሁን ያነበብከው የዝግጅት ምዕራፍ (Preparation Phase) ብቻ ነው።
ቀጣዮቹን ወሳኝ እና ሚስጥራዊ ክፍሎች ለማግኘት ሙሉውን መጽሐፍ ያውርዱ።

## በሙሉ መጽሐፍ (Full Version) ውስጥ ምን አለ?

- 📝 **ምዕራፍ 4:** አሸናፊ Motivation Letter (SOP)
- 🤝 **ምዕራፍ 5:** የ Recommendation Letter ሚስጥሮች
- 🌍 **ምዕራፍ 6-7:** ያለ IELTS እና ያለ ክፍያ የሚሰጡ ሀገራት
- 📧 **ምዕራፍ 8:** የፕሮፌሰሮች ኢሜይል (Cold Email Template)
- ✈️ **ምዕራፍ 9:** የቪዛ ሂደት እና ኢንተርቪው
- 🧳 **ምዕራፍ 10-11:** የጉዞ ዝግጅት፣ ስራ እና ኑሮ

**📥 ሙሉ መጽሐፉን አውርድ**

ወይም ወደ **ScholarshipHub.website** ይሂዱ።